# ጀግና ውለጅ እባክሽ !

አሥራደው (ከፈረንሳይ)



የምሁር መሃይም - ተባይ አላዋቂ፤
የመሃይም ኩፍስ - አስመሳይ አዋቂ፤
የጅብ ባለ ጊዜ - ታፋ መራጭ ከሽንጥ፤
ያንበሳ ልክስክስ - ልፋጭ የሚያላምጥ
የቁራ ዕርግብ መሳይ - ሠላምን አብሳሪ፤
የፈረስ አዝጋሚ - የግመል ሰጋሪ፤
ንጹህ ሰው ታሳሪ - በፈጠራ ወንጀል፤
ፍርደ ገምድል ዳኛ - ፈራጅ በቂም በቀል፤
የባዕድ ባለቤት - የነባር ባይተዋር፤
ሥልጡን ሥራ ፈቶ - ሞያ ቢስ ሲገብር፤
ልማድ ሆኖ ቀረ - አቀርቅሮ መኖር፤
በተወለድንባት በጡብያ ምድር ፡፡

ያቀረቀረ ራስ - ቀና እንዲል ካንገቱ፤
ተመልሶ እንዲከብር - የሰው ሰውነቱ፤
በፈጠራ ወንጀል - ዜጋ ሳይከሰሰ፤
ሰብዕና ተንዶ - ፍትህ ሳይገሰስ፤
ለባዕድ ተሽጦ - ሳይሟጠጥ ምድርሽ፤
ሳይሰጉ እንዲኖሩ - ተባብረው ልጆችሽ፤
በሠላም በፍቅር-  ባንድላይ በምድርሽ፤
ከወደቅሽበት ማጥ - ካዘቅት እንዲያወጣሽ፤
ጥላሸት የነካው - እንዲታደስ ክብርሽ፤
እንደ ቴዎድሮስ - እንደቋራው ልጅሽ፤
ያንድነት ምልክት - ሠንደቅ እንዲያለብስሽ፤
**እምዬ ጡብያ - ጀግና ውለጅ እባክሽ !**
**እምዬ ጡብያ - ጀግና ውለጅ እባክሽ !!**

ባርነት በቃኝ ብሎ በመነሳት፤ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት ፈር ለመቅደድ ለተነሳው፤ ለጀግናው የጎንደር ህዝብ ማስታወሻ  ትሁንልኝ፡፡
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !
እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ!!